# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
# ዓለም አቀፋዊ የምእመናን ሕብረት ድርጅት ስለ ማቋቋም

በኪዳኔ ዓለማየሁ
ሕዳር 11 ቀን 1999 ዓ/ም

## 1ኛ/ መግቢያ

የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት፤

> "...ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ሁላችሁም አንድ ንግግር እንድትናገሩ በአንድ ሐሳብ የተባበራችሁ እንድትሆኑ እንጂ መለያየት በመካከላችሁ እንዳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለምናችኋለሁ ወንድሞቼ ሆይ በመካከላችሁ ክርክር እንዳለ ስለ እናንት የቀሎኤ ቤተሰቦች አስታውቀውኛልና ይህንም እላለሁ እያንዳንዳችሁ እኔ የጳውሎስ ነኝ እኔ የአጵሎስ ነኝ እኔ ግን የኬፋ ነኝ እኔስ የክርስቶስ ነኝ ትላላችሁ። ለመሆኑ ክርስቶስ ተከፍሎአልን? ጳውሎስስ ስለ እናንተ ተሰቅሎአልን? ወይንስ በጳውሎስ ስም ተጠመቃችሁ...."
>
> 1ኛ ቆሮንቶስ ም 1 ቁጥር 10-14

1.1 በሐዋርያት ሥራ ም/8 ቁ26-39 እንደምናገኘው ኢትዮጵያውያን ክርስትናን መቀበል የጀመርነው ከሐዋርያት ዘመን ነው። ሃይማኖታችንም ጥንታዊትና ቀጥተኛ ናት።

1.2 ሐገራችንን ኢትዮጵያን በነጻነቷ ካቆዩት ሁኔታዎች አንደኛው ምክንያት ምእመናኑ ለቤተክርስቲያናቸው እና ለሃይማኖታቸው በነበራቸው ታማኝነትና መሥዋእትነት ነው።

1.3 አሁንም ቤተክርስቲያናችን ስላጋጠሟት ችግሮች የሚቆሙላት ምእመናን እንዳሏት አይጠረጠርም።

## 2ኛ/ የምእመናን ሕብረት ድርጅት ለምን ያስፈልጋል?

በዓለም አቀፍ ደረጃ እና በኢትዮጵያም ቤተክርስቲያናችንን እና ሐገራችንን እያጋጠሙ ያሉ ችግሮች እንዲወገዱ ብሎም ሰፊ ጥቅም እንዲገኝ የምእመናንን የጠነከረ ሕብረት የሚያስፈልጉ ብዙ ጉዳዮች አሉ። ከነዚህ ጥቂቶቹ፡

### 2.1 በዓለም አቀፍ ደረጃ

2.1.1 በኢትዮጵያ የራሳቸውን እምነት ለምሳሌ እስልምናን ለማስፋፋት የሚጥሩ አንዳንድ አክራሪ አገሮች በቤተክርስቲያናችን ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ በማድረግ ላይ እንዳሉ ተገንዝበናል።

2.1.2 ኢትዮጵያን በፖለቲካ እና በኢኮኖሚ (ለምሳሌ ውሀዋን) ለመቆጣጠር የሚፈልጉ ሐገሮች በቅድሚያ የሚያጠቁት የአንድነት፤ የሕልውናችን፤ እና የነጻነታችን መሠረት የሆነቺውን ቤተክርስቲያናችንን ነው።

2.1.3 በተለይ ውጪ አገር በማደግ ላይ ያሉት አብዛኞቹ ወጣቶቻችን በሕብረት ማሕበራዊ ኑሮ ተኮትኩተው ስለማያድጉ ለሌላ እምነትና ባሕል ሰለባ እየሆኑ ነው።

2.1.4 ውጪ አገሮች የምንኖረው ምእመናን ቁጥራችን እየበዛ ሔዶ በሚሊዮን ብንቆጠርም እንዲሁም ለቤተክርስቲያናችን ተቆርቋሪዎች ብንሆንም የከፋፋዮች እና የሥልጣንና የጥቅም ጥመኞች ሰለባዎች ሆነናል።

2.1.5 እንደ አሸን ለሚፈሉት ልጆቻችን የመንፈሳዊ የትምሕርት/የማሠልጠኛ ማእከል ለማቋቋም ሕብረት ያስፈልጋል።

2.1.6 እንደ ሌሎች ቤተክርስቲያኖች የኛም ከመንግሥታዊ፤ ከግላዊና ከሌሎች ድርጅቶች እርዳታ እንድታገኝ የምእመናን ሕብረት አስፈላጊ ነው።

2.1.7 ለምሳሌ ያህል የግብጽ ኮፕቶች እንደሚያደርጉት ለሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ኃይል በማቋቋም በያለበት ለሚኖረው ምእመን ሁሉ መብቱን በሕብረት የሚያስጠብቅለት አለኝታ አካል መፍጠር ይቻላል።

2.1.8 የኢትዮጵያውያንን ሕልውና ከሚያንጸባርቁት ቅርሶች አንዱ የሆነውን የኢየሩሳሌም ገዳማችንን ለመጠበቅ ሕብረት ያስፈልገናል።

2.1.9 ቤተክርስቲያናችን ጥንታዊት ብትሆንም የምእመናኖቿ ቁጥር በኋላ ከተፈጠሩት ለምሳሌ ከፕሮቴስታንቶች ጋር ሲወዳደር ኢምንት ነው። የዚህም ዋነኛው ምክንያት የስብከቱ አለመስፋፋት እና በሌሎች ቋንቋዎች ባለመጠቀም በመሆኑ ስብከቱን በዓለም አቀፍ ደረጃ አስፋፍቶ በልዩ ልዩ ቋንቋዎች በመጠቀም ለቤተክርስቲያናችንና ለሐገራችን ከፍ ያለ ጥቅም ለማስገኘት የምእመናን ሕብረት ያስፈልጋል።

2.1.10 የታሪክ ግዴታን በመወጣት ረገድ ለምሳሌ አይሑዶች የደረሰባቸውን የናዚ ግፍ ዓለም እንዳይረሳ እያደረጉ የካቶሊኩን ጳጳስ ጭምር በመደጋገም ይቅርታ እያስጠየቁ ክብራቸውንና ጥቅማቸውን ከፍ ባለ ደረጃ ያስከብራሉ። የካቶሊኮቹ ቫቲካን ፋሺሽቶችን ረድተው ስለ ተጨፈጨፉት አንድ ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያውያን ግን እስካሁን ድረስ ሐገራችን ይቅርታ አልተጠየቀችም። (ስለዚህ ጉዳይ በዚህ ጸሐፊ የተዘጋጀውን መጣጥፍ ይመልከቱ።)

## 2.2 በሐገራችን

2.2.1 በሐገራችን የምእመናንን ሕብረት የሚጠብቁ እጅግ ብዙ ችግሮች እንዳሉ የታወቀ ነው። ስለ ዋና ዋናዎቹም ዓለም አቀፋዊው የምእመናን ጉባዔ በሰፊው ተወያይቶባቸዋል። እነዚህም፤

(ሀ)በቤተክርስቲያናችን፤ በአባቶችና በምእመናን ላይ እየደረሰ ስላለው ሰቆቃ፤

(ለ) ደብሮችን ገዳማትንና የአብነት ትምህርት ቤቶችን ስለመርዳት፤

(ሐ) ስብከትን ስለማጠናከር፤

(መ) ድሕነትን ስለመቅረፍ፤

(ሠ) በቤተክርስቲያን አባቶችና ምእመናን ላይ ስለሚደርሰው ችግርና ሰቆቃ ፈጣንና ትክክለኛ ግንዛቤ ለማግኘትና ተገቢ የሆነ ዓለም አቀፋዊ እርምጃ ስለመውሰድ፤

(ረ) እርዳታው ለተረጂው ቤተክርስቲያን ወይም ሕዝብ በቀጥታ መድረሱን ስለማረጋገጥ፤

(ሰ) የሚያስተማምኑ የተቋቋሙ ምግባረ ሠናይ ድርጅቶችን በመርዳት ስለማጠናከር።

(ሸ) ቤተክርስቲያናችን በኢኮኖሚና በሌላውም ረገድ ራሷን ችላ ስለምትራመድበት ስልት ውይይቶች ተደርገዋል።

# 3. ራእይ

የድርጅቱ ራእይ በእግዚአብሔር ቸርነትና እርዳታ ምእመናን የተሟላ ሕብረት ፈጥረን በምናከናውነው ጥረት ቤተክርስቲያናችን ተጠናክራ በኢትዮጵያም ሆነ በዓለም በሙሉ ተስፋፍታ ለማየት ነው።

# 4. መሠረታዊ መመሪያዎችና ዓላማዎች

## 4.1 መሠረታዊ መመሪያዎች

(ሀ) የድርጅቱ ወገንተኝነት ለቤተክርስቲያናችን ብቻ ነው። በዘር፤ በዜግነት፤ በጾታ፤ በፖለቲካ፤ በቤተክሕነት ሽኩቻና በመሳሰለው መለያየት አይኖርም።

(ለ) ዶግማና ቀኖና ውስጥ አይገባም። ቢሆንም ምእመናንን በሚመለከቱ ከባድ ጉዳዮች (ለምሳሌ ስለ ቁርባን) አባቶችና ምሑራን በማጥናትና በመመካከር ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ማነሳሳት ይቻላል።

(ሐ) ምእመናን የቤተክርስቲያን አለኝታዎች በመሆናችን ችግሮቿን የመወጣት ኀላፊነት አለብን።

(መ) ቤተክርስቲያናችንን በማጠናከር ሐገራችንንም እየደገፍን መሆኑን መገንዘብ አለብን።

4.2 ዓላማዎች

(ሀ) የሩቅ ዓላማዎች

1ኛ/ ቤተክርስቲያናችንና ሐገራችን ከተጋረጡባቸው የአክራሪ እስላም አገሮች የቀውስ ስልት እንዲድኑ በሕብረት ታግሎ ኢትዮጵያን ማዳን፤

2ኛ/ የቤተክርስቲያናችን ደብሮችና ገዳማት በተቀላጠፈ የልማት ስልት በመጠቀም ራሳቸውን እንዲችሉና በሐገራችንም ያለውን የድህነት ስቃይ ለመቅረፍ አስ ተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ማድረግ፤

3ኛ/ በኢትዮጵያ ያሉት የአብነት ት/ቤቶችና የሥልጠና ማእከሎች ተጠናክረው እንዲሁም አዳዲሶች ተቋቁመው ብቁ የሆኑ የሃይማኖት መሪዎችና አስተማሪዎች በብዛት እንዲ ፈልቁ ማድረግ፤

4ኛ/ የቤ/ክርስቲያናችን ስብከት ተጠናክሮ በልዩ ልዩ ቋንቋዎች በመጠቀም ለምሳሌ በእ ንግሊዝኛ፤ በፈረንሳይኛ፤ በስፓኒሽ፤ ወዘተ የቤተክርስቲያናችን እምነት በዓለም በሙሉ እንዲሰራጭ ማድረግና በዚያውም ለሐገራችን ሰፊ ድጋፍ ማስገኘት፤

5ኛ/ የቤተክርስቲያን ቅርሶች የኢየሩሳሌም ገዳማችን ጭምር በመልካም እንክብካቤ እንዲጠበቁልን ማድረግ፤

6ኛ/ በምእመናን መሀል እንዲሁም ከአባቶች ጋር ያለው ፍቅር፤ ሰላምና አንድነት ዳብሮ ከሥልጣንና ከጥቅም ሽኩቻ ርቀን ለቤተክርስቲያናችንና ለሐገራችን የዘለቄታ ልማትና ጥንካሬ እንዲከሰት ማድረግ፤

(ለ) የአጭር ጊዜ ዓላማ

የረጅም ጊዜ ዓላማውን ለማስገኘት ጥናቶችን ለማከናወን፤ ለዘለቄታ የሚቋቋመውን መዋቅርና መተዳደሪያ ደንብ ማዘጋጀት፤ እንዲሁም አንዳንድ ተጨባጭ እርዳታ ዎችን በሕብረት ማመቻቸት።

5. የሚያስፈልገው መዋቅር

5. 1 ለዘለቄታው መዋቅር መንደርደሪያ ሀሳቦች

በየሁለት ዓመት የሚከናወን የምእመናን ጠቅላላ ጉባዔ (ከየሐገሩ በተመረጡ አባሎች)

የምእመናን የበላይ ኮሚቴ (በጠቅላላ ጉባዔው የሚመረጥ)

ለምእመናን ጠቅላላ ጉባዔ ተጠሪ የሆኑ

-አስመራጭ ኮሚቴ (በጉባዔው የሚመረጥ)

-ተቆጣጣሪ ኮሚቴ (በጉባዔው የሚመረጥ)

-የሽምግልና ኮሚቴ (በጉባዔው የሚመረጥ)

ዋና ሥራ አስኪያጅ (በጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጥ)

ለዋና ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ የሆኑ (በበላይ ኮሚቴ የሚመረጡ)

-የስትራተጂ፣ እቅድና በጀት ኮሚቴ
-የሕዝብ መገናኛ ክፍል
-የአስተዳደር እና የሂሳብ ዘርፍ
-የአክራሪ እስላም አገሮች ጉዳይ አጥኚ ኮሚቴ
-ለኢትዮጵያ ደብሮች እና ገዳማት የድጋፍ ኮሚቴ
-ለአብነት ት/ቤቶች የድጋፍ ኮሚቴ
-በእሥራኤል ላሉ የኢትዮጵያ ደብሮች እና ገዳማት የድጋፍ ኮሚቴ
-የስብከት ኮሚቴ (በኢትዮጵያ)
-የስብከት ኮሚቴ (በውጪ አገሮች)
-የስብከት ኮሚቴ (በውጪ አገሮች ቋንቋዎች)
-የወጣቶች ጉዳይ ኮሚቴ
-የድጋፍ/እርዳታ ማሰባሰቢያና የልማት ኮሚቴ
-የትምሕርት ማእከል ኮሚቴ
-የቤ/ክያናችን ቅርሶች ጉዳይ ኮሚቴ

5.2 የሽግግር ኮሚቴ (2-3 ዓመት)
በዓለም አቀፋዊው የምእመናን ጉባዔ የሚመረጡ (ከ7-10 ሰዎች)

<u>ዋና ዋና ተግባሮች</u>

5.2.1 ዝርዝር ጥናት በማከናወን የቅርብና የሩቅ ዓላማዎችን ለመተግበር ተገቢ የሆነ ስትራተጂ፣ እቅድና መዋቅር ከነመተዳደሪያ ደንቡ ማዘጋጀትና በምእመናን መሀል ሰፊ ግንዛቤና ተቀባይነት እንዲኖረው፣ እንዲሁም ከቀረጥ ነጻ በሆነ አካልነት እንዲመ ሠረት ማድረግ፣

5.2.2 በየሐገሩ እንደ አስፈላጊነቱም በየክፍለ ሐገሩና በየከተማው ድርጅቱን የሚደግፉ ኮሚቴዎች ተቋቁመው በትጋት እንዲሠሩ ማድረግ፣

5.2.3 በምእመናን ሕብረት ለተቸገሩ ልዩ ትኩረት ለሚገባቸው ደብሮችና ገዳማት እንዲሁም ለአብነት ት/ቤቶች እርዳታ ማድረግ፣

5.2.4 የኢየሩሳሌም ገዳም ቅርሳችንን ለመጠበቅ ልዩ ግብረ ኃይል በማቋቋም የሚያስፈል ገውን ድጋፍ ማበርከት፣

5.2.5 አክራሪ የእስላም አገሮችና ነውጠኛ ተከታዮቻቸው በቤተክርስቲያናችን ላይ ስለሚ ያከናውኑት መሠሪ ተግባር በምእመናን መሀል ሰፊ ግንዛቤ እንዲኖር ማድረግና ተ ገቢ ስልት ቀይሶ በመቋቋም ክርስቲያኑና እስላሙ ሕዝብ በሰላም እየኖረ ዋናውን ጠላቱን ድህነትን ካገራችን እንዲያጠፉ በትጋት እንዲተባበር ማድረግ፣

5.2.6 ስለ አንዳንድ መሠረታዊ ለቤተክርስቲያን አስፈላጊ ጉዳዮች ለምሳሌ በውጪ ሐገ ሮች መቋቋም ስለሚገባቸው የትምሕርት ማእከሎችና ፕሮግራሞች፣ የቤተክርስቲ ያናችንን ቅዳሴና ትምሕርት በእንግሊዝኛ ስለ ማቅረብ፣ የእስላም አገሮች በኢት

ዮጵያ ስለሚያደርጉት እንቅስቃሴ፤ ወጣቶቻችን ወደ ቤተክርስቲያናችን ለዘለቄታው ተጠግተው ስለሚቆዩበት ስልት፤ ወዘተ በሁነኛ ምሑራን ጥልቅ ጥናቶች እየተደረጉ ግኝቶቹ ለምእመናን እንዲደርሱና ተጨባጭ እርምጃዎች እንዲከናወኑ ማመቻቸት፤

5.2.7 በምእመናን መሀል ጥልቅ መግባባት እንዲኖር መቋቋም ስለሚያስፈልጉ የመገናኛ ብዙኅን ዘዴዎች የድረ ገጽ ስለ ማቋቋም ጭምር ማጥናትና ሥራ ላይ ማዋል፤
5.2.8 በቤተክርስቲያናችን አባቶች እንዲሁም ምእመናን መሀል የተከሰተውን ጠንቀኛ መከፋፈል ለማስወገድና በሕብረትና በሰላም ለአንዲት ቤተክርቲያናችንና ለሐገራችን በትጋት እንድንሠራ የተቀናጀ ጥረት ለማድረግ ልዩ ግብረ ኃይል ማቋቋም።
5.2.9 የምክክር ስብሰባዎችን እንደ አስፈላጊነቱና አቅም እንደ ፈቀደ ማከናወን፤
5.2.10 የአስተዳደሩና የሂሳብ ሥራው በግልፅነትና በጥብቅ ቁጥጥር እንዲከናወን አድርጎ ተግባሩ ሁሉ በዲሞክራሲ ስልት እንዲፈጸም ማድረግ፤
5.2.11 ተግባሮቹ ሁሉ በጸደቀው ፕሮግራም መሠረት ምን ደረጃ እንደ ደረሱ በድርጅቱ ድረገጽና በመገናኛ ብዙኅን ቢያንስ በየሶስት ወሩ እና በየዓመቱ መግለጽ፤

<u>የሽግግር ኮሚቲው ፍጻሜ</u>

የአጭር ጊዜውን ተግባሮች በ2-3 ዓመት ውስጥ አጠናቅቆ ሁለተኛውን ዓለም አቀፋዊ የም እመናን ጉባዔ አዘጋጅቶ ሌላ ምርጫ ይከናወንና የሽግግር ኮሚቲው ሕልውናና ተግባር ይቋረጣል።

## 6. <u>መደምደሚያ</u>

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሚቆሙላት ነገሥታቱ፤ የመንፈሳዊ አባቶች እና ምእመናኑ ነበሩ። የዘመኑ አገዛዝ ስልት ሌላ ነው። የመንፈሳዊ አባቶችም መተባበር አልቻሉም። ምእመናንም በሕብረቱ መዛባት ኃላፊነት አለብን። ቢሆንም ስህተታችንን አርመን ቤተክርስቲያናችንን ካልጠበቅን ሐገራችንንም ጭምር የሚያሰጋ ሁኔታ ሊያጋጥም እንደሚችል የታወቀ ነው። ቄስ ሲታረድ፤ ቤተክርስቲያን ሲቃጠል፤ ደብሮች በችግር ምክንያት ሲዘጉ፤ ኢየሩሳሌም ያሉ መነኮሳቶቻችን ሲደበደቡ፤ የአብነት ት/ቤቶች በመዳከማቸው ተማሪዎች ሲበተኑ፤ የቤተክርስቲያን ቅርሶች ሲበዘበዙ የሚቆጨን ከሆነ ከእንቅልፋችን ልንባንን ይገባል። ስለዚህ በጊዜ ነቅተን በቤ/ክርስቲያናችንና በሐገራችን ላይ ያንዣበቡትን ከባድ ጠንቆች ለመቋቋም አሁኑኑ ተባብረን መነሳት አለብን። ይህንን ከፍተኛና ክቡር ዓላማ በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የም እመናን ሕብረት ድርጅት ማቋቋም እጅግ አስችኳይ እና አስፈላጊ ጉዳይ ነው።

ቸሩ እግዚአብሔር ሕብረቱን ትጋቱንና ብርታቱን ይስጠን።

እግዚአብሔር ይስጥልኝ።